ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የሰ/መ/ቁ 46075 ችሎቱ በሰ/መ/ቁ 14414 የሰራውን ስህተት የሚያርም ከመሆኑም በላይ በሁለቱም መዝገቦች የህግ ትርጉም ከተሰጠበት የጊዜ ልዩነት አንጻር የኋለኛውን መዝገብ (ሰ/መ/ቁ 14414) የመሻር ውጤት እንዳለው ተደርጎ መተርጎም ይኖርበታል፡፡

### ሥራ ተቋራጭ

### የኃይማኖት ተቋም ሠራተኞች

የኃይማኖት አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች የሚያቀርቡት የሥራ ክርክር የፍርድ ቤቶችን ደጃፍ አጣቦ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ የኃይማኖት ተቋማትም ዕለታዊውን ኃይማኖታዊ ተግባራቸውን ከማከናወን በተጨማሪ ከተቋሙ አገልጋዮች ጋር በመሟገት ትንሽ የማይባል ጊዜያቸውን ማጥፋት ግድ ሆኖባቸው ነበር፡፡ ጉዳዩ ከኃይማኖት ነፃነት ብሎም ከኃይማኖትና መንግስት መለያየት ጋር ተያይዞም ህገ መንግስታዊ ጥያቄ አስነስቷል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ የኃይማኖት አገልግሎት በሚሰጡ ሠራተኞች ላይ ያለውን ተፈፃሚነት በሚመለከት በተለያየ ጊዜ በብዙ ፍርድ ቤቶች የተዘበራረቀ አቋም የሚያዝበት ነጥብ ነበር፡፡ አከራካሪው ነጥብ በሰበር መቋጫ ያገኘው ግንቦት 4 ቀን 1998 ዓ.ም በሰ/መ/ቁ 18419 በተሰጠ ውሳኔ ሲሆን ይኸው ውሳኔ ለስር ፍርድ ቤቶች ብቻ ሳይሆን ለሰበር ችሎቱ ጭምር ለቀጣይ ተመሳሳይ ጉዳዮች መሰረት ለመጣልና ተጠቃሽ ለመሆን በቅቷል፡፡

ክርክሩ የቀረበው በአመልካች የሐመረ ወርቅ ቅ/ማሪያም ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እና መልስ ሰጭዎች እነ ዲያቆን ምህረት ብርሐን (6 ሰዎች) *(ግንቦት 4 ቀን 1998 ዓ.ም. ሰ/መ/ቁ 18419 ቅጽ 8)* ሲሆን የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይም ከሥራ ውል ማቋረጥ ጋር የተያያዘ ነበር፡፡ መልስ ሰጭዎች በአመልካች ተቋም ለመንፈሳዊ አገልግሎት ተቀጥረን ስናገለግል ቆይተን ከህግ ውጭ የተሰናበትን በመሆኑ ወደ ሥራ እንድንመለስ በማለት

በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱም የአዋጅ ቁ.42/85 ድንጋጌዎችን ተፈፃሚ በማድረግ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ በኃላ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ ሆኖም የሰበር ችሎት ጉዳዩን ከመረመረ በኃላ በመንፈሳዊ ሥራ ግንኙነት ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ክርክር በአዋጅ ቁ. 42/85 እንደማይሸፈንና የሥራ ክርክር አካላትም እነዚህን መሰል ጉዳዮች አይቶ ውሳኔ የመስጠት የዳኝነት ስልጣን እንደሌላቸው አስረግጦ በማብራራት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔዎች ሽሮታል፡፡

ችሎቱ በውሳኔው ላይ እንዳመለከተው የሥራ ክርክር ሰሚ አካላት መንፈሳዊ የሥራ ግንኙነቶች ላይ ተመስርተው የሚነሱ ክርክሮችን በአዋጅ ቁጥር 42/85 መሰረት አይተው የመወሰን ስልጣን የሌላቸው ሲሆን ክርክሮቹ የኃይማኖት ተቋማቱ በሚኖራቸው አለመግባባቶች በሚፈቱበት መንገድ የሚታዩ ናቸው፡፡ በችሎቱ የህግ አተረጓጎም በሀይማኖት ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች በሁለት ተከፍለዋል፡፡ እነዚህም፤

- የሀይማኖት ተቋሙ ከሚከተለው እምነትት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለውና ከእምነቱ ተነጥሎ ሊታይ የማይችል መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞች
- የሚሰጡት አገልግሎት ከእምነቱ ጋር ያልተቆራኘ ሠራተኞች

በሰ/መ/ቁ 18419 በተሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት በመጀመሪው ረድፍ ውስጥ የተመደቡት ሠራተኞች ከተቋሙ ጋር በሚኖራቸው የመንፈሳዊ የሥራ ግንኙነት የሚያስነሳቸው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች ከእምነቱ ተነጥለው የሚታዩ ባለመሆናቸው በሥራ ግንኙነቶቹ ውስጥ ጠልቆ መግባት በእምነቱ ውስጥ ጠልቆ መግባትን ያስከትላል፡፡ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስልጣንን አስመልክቶም ችሎቱ እንዳለው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 3(3) ለ መሰረት የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ተፈፃሚ እንዳይሆን ደንብ የሚያወጣው በሁለተኛው ረድፍ ለተመለከቱት ሠራተኞች እንጂ በመጀመሪያው ረድፍ ውስጥ ለተመደቡት ሠራተኞች አይደለም፡፡ ለእነዚህ ደንብ የሚያወጣ ከሆነ መንግስትና ሀይማኖት የተለያዩ ናቸው፤ መንግስት በሐኃይማኖት ጉዳዩች ጣልቃ አይገባም በማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 11 ከተደነገገው ጋር የሚጋጭ ይሆናል፡፡

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአዋጁ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከሃያ ዓመታት ዝምታ በኂላ የካቲት 30 ቀን 2007 ዓ.ም. ሲጠበቅ የነበረውን ደንብ አውጥቷል፡፡ ይህ ደንብ "የሃይማኖት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በቅጥር

ላይ የተመሠረቱ የሥራ ግንኙነቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ. 342/2007 ዓ.ም.” የሚል ርዕስ የተሰጠው ሲሆን የአዋጁን ተፈጻሚነት በሁለት መልኩ ገድቦታል፡፡ ይኸውም አንደኛ የተወሰኑ ሠራተኞች የሚሰጡት አገልግሎት መንፈሳዊነት ከግምት ውስጥ ገብቶ ከአዋጁ ተገለዋል፡፡[45] ሁለተኛ በአዋጁ የሚታቀፉትም ቢሆኑ የደመወዝ ጭማሪ፣ ልዩ ልዩ ጥቅሞችና በመሳሰሉት ጉዳዮች የኅብረት ድርድር የማድረግ መብት ተነፍገዋል፡፡[46]

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣው ደንብ ቁ. 342/2007 ለሰበር ችሎት አቋም የህግ መሰረት በመጣል በችሎቱ የተሰጠውን የህግ ትርጉም ወደ ተጻፈ ህግ ቀይሮ አጽንቶታል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ በሃይማኖት ድርጅቶች ውስጥ መንፈሳዊ አገልግሎት በሚሰጡ አገልጋዮች ላይ ተፈጻሚነት እንደሌለው በደንቡ አንቀጽ 3(1) ላይ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን ይህም ከአገላለጽ ጀምሮ በሰ/መ/ቁ 18419 የተሰጠው የህግ ትርጉም ግልባጭ ነው፡፡ ከዚህም አልፎ ደንቡ በአንቀጽ 2(1) ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሰጠው ትርጓሜ ሙሉ በሙሉ ከሰ/መ/ቁ 18419 ተቀድቶ የተወሰደ ነው፡፡ በድንጋጌው መሰረት መንፈሳዊ አገልግሎት ማለት “በሃይማኖት ድርጅት ውስጥ ከእምነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን መንፈሳዊ ተግባራትን ብቻ ማከናወን” ማለት ነው፡፡

የደንብ ቁ. 342/2007 አዋጁ ተፈጻሚ የማይሆንባቸውን የሃይማኖት ድርጅት ሠራተኞች ከማመልከት በተጨማሪ ተፈጻሚ የሚሆንባቸውንም ለይቶ አስቀምጧል፡፡ በዚሁ መሰረት በሃይማኖት ድርጅቶች ውስጥ በገቢ ማስገኛ ሥራዎች እና በአስተዳደራዊ ወይም በበጎ አድራጎት ተግባራት የተሰማሩ ሠራተኞች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 የተፈጻሚነት ወሰን ውስጥ ተካተዋል፡፡ ቅይጥ ሚና ሲኖር ማለትም መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ወይንም መንፈሳዊና የበጎ አድራጎት ተግባር በአንድ ሰው በጣምራ ከተከናወነ አዋጁ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ የኅብረት ድርድርን በተመለከተ የሃይማኖት ድርጅት በሁሉም ጉዳዮች ላይ ድርድር ለማድረግ የሚገደደው በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ ከተሰማሩት ሠራተኞች ጋር ብቻ ሲሆን ከተቀሩት አዋጁ ተፈጻሚ ከሚሆንባቸው ሠራተኞች ጋር ግን የደመወዝ ጭማሪ፣ ልዩ ልዩ ጥቅሞች፣ ማበረታቻዎችና የመሳሰሉትን በተመለከተ ድርድር ለማድረግ አይገደድም፡፡

---

[45] ደንብቁ. 342/2007 ዓ.ም. አንቀጽ 3(1)

[46] ደንብቁ. 342/2007 ዓ.ም. አንቀጽ 4

## *መንፈሳዊ አገልግሎት ምንድነው? መለኪያውስ?*

በሰ/መ/ቁ 18419 እና በቀጣይ በሰበር ችሎት በተሰጡት ውሳኔዎች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ውስጥ አይካተቱም የተባሉት ሁሉም የኃይማኖት ተቋም ሠራተኞች ሳይሆኑ መንፈሳዊ ወይም ሃይማኖታዊ ተግባራትን የሚያከናውኑት ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህ ሠራተኞች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ቁ.342/2007 በግልጽ አግልሏቸዋል፡፡ ለመሆኑ መንፈሳዊ ወይም ኃይማኖታዊ አገልግሎት ምንድነው? መለኪያውስ? በሰ/መ/ቁ 18419 የሰበር ችሎት ተፈጻሚ ባደረገው መለኪያ ኃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያከናውኑ ሠራተኞች "የሚሰጡት አገልግሎት የኃይማኖት ተቋሙ ከሚከተለው እምነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለውና ከእምነቱ ተነጥሎ ሊታይ የማይችል" በሚል ተገልጸዋል፡፡ ይኸው አገላለጽ ይዘቱ ሳይቀየር በደንብ ቁ. 342/2007 የመንፈሳዊ አገልግሎት መደበኛ ትርጓሜ ሆኗል፡፡

በአገልግሎት (የሥራ ተግባራት) እና በእምነት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩን ለመወሰን ክሱን ያቀረበው ወገን በኃይማኖት ተቋሙ ውስጥ ያለው ሚና፤ የሚያከናውናቸው ተግባራትና እነዚህ ተግባራት በእምነቱ ውስጥ ያላቸው ቦታ ከብዙ በጥቂቱ መዳሰስ ያለባቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ የሰበር ችሎት በተወሰኑ መዝገቦች በዚህ መልኩ ፍተሻ እያደረገ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም በአንዳንድ መዝገቦች ላይ ግን መንፈሳዊ አገልግሎት ስለመኖሩ አመላካች ሁኔታዎች በሌሉበት አዋጁ ተፈጻሚነት እንደሌለው ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ በሰ/መ/ቁ 47806 *(አመልካች የሆህተሰማይ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲየን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እና ተጠሪ ዲያቆን አያሌው አዲሱ ታህሳስ 20/2002 ዓ.ም. ቅጽ 9)* ተጠሪ በዲቁና ሲያገለግሉ እንደነበር በክሳቸው ላይ የገለጹትን መነሻ በማድረግ ችሎቱ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት ኃይማኖታዊ እንደሆነ አቋም ይዞበታል፡፡ በሰ/መ/ቁ 21439[47] እና 51071[48] እንዲሁ የሥራ ተግባራት ከግምት ውስጥ ገብቶ መንፈሳዊ አገልግሎት ስለመሆኑ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ይሁን እንጂ በሰ/መ/ቁ 38331፤[49] 41508፤[50]

[47]አመልካች የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት እና ተጠሪ መልዐከፀሐይ ዳንኤል ተስፋዬ ግንቦት 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ያልታተመ

[48]አመልካች የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ጠ/ቤተ ክህነት ተጠሪ ሊቀጠበብት ታደሰ ውቤ ሰኔ 22 ቀን 2002 ዓ.ም. ያልታተመ

[49]አመልካች በኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በባሌ ሐገረ ስብከት የጎባ ቅዱስ ገብርዔል ቤተክርስቲያን እና ተጠሪ መርጌታ መርዓዊ ስዩም የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም. ያልታተመ

[50] አመልካች የኢት/ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ጉጂ ቦረና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት እና ተጠሪ መላከሕይወት አባ ኃ/ማርያም ሚያዝያ 14 ቀን 2001 ዓ.ም. ያልታተመ

© አብርሃም ዮሃንስ ኃይሉ 2008 ዓ.ም. ድሬዳዋ www.chilot.me

20070[51] እና 21086[52] በችሎቱ ውሳኔ መግቢያ ላይ "ተጠሪ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን…" በሚል ከመስፈሩ በስተቀር በምን መለኪያ መንፈሳዊ ሊባል እንደቻለ፤ ሥራውና ተግባራቱስ ምን እንደሆኑ የሚጠቅም ነገር የለም፡፡

በሰ/መ/ቁ 34440 *(አመልካች መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና ተጠሪ መጋቢ ሚስጢር መዝገቡ በላይነህ ሰ/መ/ቁ 34440 ጥቅምት 06 ቀን 2001 ዓ.ም ያልታተመ)* የ'ቀጥተኛ ግንኙነት' ፍቺ ራሱን ችሎ በጭብጥነት የወጣ ሲሆን ችሎቱ ግን ፈታኝ ለሆነው ጥያቄ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ከጭብጡ መሸሽን መርጧል፡፡ የጉዳዩ መነሻ ተጠሪ በቅኔ እና አቋቋም መምህርነት ሲያገለግሉ እንደነበር በመግለጽ ያቀረቡት ክስ ሲሆን አመልካችም በመልሱ ተጠሪ የሚሰጡት አገልግሎት መንፈሳዊ ስለሆነ በአዋጁ አይሸፈኑም በማለት መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ መቃወሚያው ክሱን በሰማው ፍርድ ቤት እና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ቢያጣም የሰበር ችሎቱ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የቅኔ መምህርነት አገልግሎት መንፈሳዊ በመሆኑ ጉዳዩ በሥራ ክርክር ሰሚ አካላት ሊታይ እንደማይገባ በመግለጽ አመልካች ያቀረበውን መከራከሪያ ተቀብሎታል፡፡ ክሱን መጀመሪያ ያየው ፍርድ ቤት የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው የተጠሪ አገልግሎት ከኃይማኖት ተቋሙ ጋር የተያያዘ ቀጥተኛ መንፈሳዊ ሥራ እንደማይባል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ነው፡፡

በሰበር በነበረው ክርክር ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት የመታየቱ አግባብነት በጭብጥነት ተይዞ የተመረመረ ሲሆን ጭብጡን ለመፍታት የቅኔ መምህርነት ከአገልግሎቱ ባህርይ አንጻር ከኃይማኖቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በቅድሚያ ምላሽ ማግኘት ነበረበት፡፡ ችሎቱ ይህንን መሰረታዊ ጥያቄ የነካከው ቢሆንም የህግ ትርጉም ሳይሰጥበት አልፎታል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ በሐተታው ላይ የሰፈረውን ማየቱ ጠቃሚ ነው፡፡

> *"ተጠሪ ለዚህ ሰበር ችሎት በሰጡት መልስም የቅኔ መምህርነት ከኃይማኖት ተቋሙ ጋር የተያያዘ ቀጥተኛ መንፈሳዊ ስራ አይደለም በማለት ያነሱት ክርክር የለም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የቅኔ መምህርነት ስራ ቀጥተኛ የሆነ መንፈሣዊ ስራ መሆኑ የሚያከራክር ሆኖ አልተገኘም፡፡"*

[51] አመልካች የጉጉማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤ/ክርስትያን ሠበካ ጉባዔ እና ተጠሪ መምሬ አንዳርጌ አበጀ ግንቦት 4 ቀን 1998 ዓ.ም. ያልታተመ

[52] አመልካች የቀጨኔ ደብረ ሠላም መደኃኔዓለም ቤ/ክርስትያን አስተዳደር እና ተጠሪ መምሬ ምስጋናው አሰፋው ግንቦት 4 ቀን 1998 ዓ.ም. ያልታተመ

ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ ሲያከራክር የነበረውና አመልካችና ተጠሪ በግልጽ የተለያዩበት ብሎም የተከራከሩበት ይህ መሰረታዊ ነጥብ በደፈናው "የሚያከራክር ሆኖ አልተገኘም" በሚል ታልፎ ውሳኔ መስጠቱ ሲታይ ችሎቱ ፈታኙን ጥያቄ ከመጋፈጥ ይልቅ መሸሸን እንደመረጠ ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ በኃይማኖት ተቋም ውስጥ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው የሚያከናውነው ተግባር ከእምነቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው/የለውም ብሎ ለመወሰን ተግባራቱን በእምነቱ መነጽር ማየት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ ህገ-መንግስታዊ የኃይማኖትና መንግስት መለያየት ጥያቄ የሚያስነሳ ከመሆኑም በላይ አግባብነት ያለው በቂ ኃይማኖታዊ ዕውቀትን ይጠይቃል፡፡ የኃይማኖት ተቋሙ መንፈሳዊ ብሎ የፈረጀውን አገልግሎት መደበኛ ፍርድ ቤት መንፈሳዊ አይደለም ብሎ አቋም ከያዘበት ህገ-መንግስታዊ ጥያቄው ፈጦ ይወጣል፡፡ ለዚህም ነው ጭብጡ ፈታኝ ነው የተባለው፡፡

### የዳኝነት ስልጣን

የሥራ ክርክር ሰሚ አካላት መንፈሳዊ የሥራ ግንኑነቶች ላይ ተመስርተው የሚነሱ ክርክሮችን አይቶ ለመወሰን የዳኝነት ስልጣን እንደሌላቸው የሰበር ችሎት በዋነኝነት ያሰመረበት ነጥብ ነው፡፡ መሰረታዊ ጉዳዩ የዳኝነት ስልጣን ከሆነ በዚህ ነጥብ ላይ ከተከራካሪዎች መቃወሚያ ቢቀርብም ባይቀርብም ጉዳዩ የቀረበለት የዳኝነት አካል በራሱ አነሳሽት ስልጣን የለኝም ብሎ መዝገቡን መዝጋት ይኖርበታል፡፡ *(አመልካች ግሎባል ኮምፕዩቲንግ ሶሉሽንስ ኃ/የግ/ማህበር እና ተጠሪ እነ አቶ ዳዊት ሞገስ (7 ሰዎች) ሰ/መ/ቁ 36983 ታህሳስ 2 ቀን 2001 ዓ.ም. ያልታተመ)* በሰ/መ/ቁ 18419 ላይ የስር ፍርድ ቤቶች ስልጣን የላቸውም የሚል መቃወሚያ ስለመቅረቡ የተገለፀ ነገር የለም፡፡

ይሁን እንጂ ክሱን ያቀረበው ወገን ሃይማኖታዊ ተግባራትን እንደሚያከናውን በሃይማኖት ተቋሙ በኩል ካልተገለጸና ደጋፊ ማስረጃና ክርክር ካልቀረበ ፍርድ ቤት ስልጣኑን አስመልክቶ የሚሰጠው ውሳኔ በተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ላይ መሆኑ ቀርቶ በግምት እና በመላምት ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ በአገሪቱ የተለያዩ የእምነት ተቋማት የሚገኙ እንደመሆናቸው መንፈሳዊ ወይም ሃይማኖታዊ አገልግሎት ይዘቱ እንደየተቋማቱ መለያየቱ አይቀርም፡፡ ስለሆነም የአገልግሎቱ ዓይነት ፍርድ ቤት ግንዛቤ የሚወስድበት ነጥብ ሊሆን አይገባም፡፡

በአመልካች መርጌታ ልሳነወርቅ ብዙነህ እና ተጠሪ ጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት *(ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም. ሰ/መ/ቁ 32229 ቅጽ 6)* መካከል በነበረው ክርክር አመልካች በተጠሪ ጽ/ቤት የኦጋዴን ሐገረ ስብከት ሥራ

አስኪያጅ መሆናቸውን በግልፅ በማመልከት በስር ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡ ሲሆን በሰበር በነበረው ክርክር ችሎቱ የዳኝነት እንዳልተሰጠው ገልጾ መዝገቡን አልዘጋውም፡፡ በመዝገቡ ላይ አመልካች ሃይማኖታዊ አገልግሎት የሚያከናውኑ ስለመሆኑ በተጠሪ የቀረበ መቃወሚያ የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሆነ አስቀድሞ ጉዳዩን ያየው የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ብሎም የሰበር ችሎት በራሳቸው አነሳሽነት መዝገቡን አለመዝጋታቸው አመልካች ኃይማኖታዊ ተግባር እንደማያከናውኑ ስለተቀበሉት ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ተጠሪ መቃወሚያ ባለማቅረቡ በዝምታ ማለፋቸው ግን ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት የዳኝነት ስልጣን የለኝም ብሎ መዝገቡን ሊዘጋው የሚገባው ክሱን ያቀረበው ወገን በግልጽ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ እንደነበረ ወይም ለዚሁ ተግባር እንደተቀጠረ በክስ አቤቱታው ላይ ካመለከተ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ከላይ በሰ/መ/ቁ 36983 የተሰጠው የህግ ትርጉም ከአዋጁ ተፈጻሚነት ወሰን ጋር ተያይዞ በሚነሳ በተለይ መንፈሳዊ አገልግሎትን ያማከለ የስልጣን ጥያቄ ላይ ተፈጻሚነት ማድረጉ ተገቢነት የለውም፡፡

### የበጎ አድራጎት ድርጅት ሠራተኞች

ደንብ ቁ. 342/2007የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚመሰርቱትን ግንኙነት በተመለከተ ግልጽ በሆነ አነጋገር የትኞቹ ሠራተኞች ከአዋጁ እንደተገለሉ ከማመልከት ይልቅ አደናጋሪ በሆነ አገላለጽ አዋጁ ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን ሠራተኞች ለይቶ ለማስቀመጥ ሞክሯል፡፡ በአንቀጽ 4 ላይ እንደተመለከተው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 በሚከተሉት የበጎ አድራጎት ድርጅት ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚነት አለው፡፡

- የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ገቢ ለማግኘት በሚያቋቁሟቸው ድርጅቶች ውስጥ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ በተሠማሩ ሠራተኞች
- በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ አስተዳደራዊ ወይም የበጎ አድራጎት ተግባርን ለማከናወን በተሠማሩ ሠራተኞች

በደንቡ አንቀጽ 2(2) የበጎ አድራጎት ድርጅት ትርፍ የማግኘት ዓላማ የሌለው ሰብዓዊ፤ ማኅበራዊ ወይም የልማት አገልግሎት ለሕዝብ ለማበርከት የተቋቋመ ድርጅት ወይም ማኅበር እንደሆነ ትርጓሜ የተሰጠው ሲሆን ገቢ ማስገኛ ሥራ ማለት ደግሞ የሃይማኖት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅት ገቢ ለማግኘት ባቋቋመው ድርጅት ሥር የሚከናወን ዕቃዎችን የማምረት ወይም የማከፋፈል፤ አገልግሎት የመስጠት ወይም ሌላ መሰል የገቢ ማስገኛ ሥራ ነው፡፡ ሆኖም አስተዳደራዊ እና የበጎ አድራጎት ተግባራት የትኞቹን ተግባራት